# መጀመሪያ መቀመጫዬን

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

*ማን "መጀመሪያ መቀመጫዬን" እንዳለ አንባቢ የሚያስታውስ ይመስለኛል። አዎ እንደምታውቁት የዝንጀሮ አስተዋይ ነው። እንግዲህ ዝንጀሮ እንኳን በአቅሙ ቅድሚያ መሰጠት ያለባቸውን ጉዳዮች አንጠርጥሮ ያውቃል ማለት ነው። ምናልባት ዝንጀሮ ይህንን ያለበትን ምክንያት የዘነጋችሁ ካላችሁ እኔ በማውቀው መሰረት ነገሩ እንደዚህ ነው። መቼም ይህ ሰው የተባለ ፍጡር ይህችን አለም ለራሱ እያመቻቸ ሌሎችን ፍጡራን መጋፋት ከጀመረ ውሎ አድሯል። በመሆኑም እንኳን ሜዳውን ቀጥ ብሎ የቆመውን አፋፍና ዳገትም እያረሰ እንደ ዝንጀሮ ያሉትን ተፈጥሮን አምነው የሚኖሩትን እንስሳት የሚልሱትና የሚቀምሱት አሳጥቷቸው ቁጭ ብሏል። እንደዚህ እኛን ወደ ምእራቡ፤ ወደ አረቡና ሌሎችም በድህነት ወደሚታወቁት የአፍሪካ አገሮች ሳይቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለስደት እንደዳረገን ክፉ አገዛዝ ሁሉ እነርሱንም የራሱን ምቾት ብቻ የሚያይ ሰው ከለመዱት ቅዬ እያባረረ ባለመዱት ቦታ በባይተዋርነት ማስኖሩን ቀጥሏል።*

*ከእለታት አንድ ቀን ኑሮውን ለመግፋትና ልጆቹንም ቀልቦ ለማደር ከገደል ገደል የሚዘል ዝንጀሮ  በሰው ልጅ ተንኮል ምክንያት ተገፍትሮ ለርሃብ በመዳረጉ የሰውን ልጆች ድርጊት እያማረራ እሸት ፈልቅቆ ሊያመጣ አጥር ሰብሮ ከበቆሎ ሰብል ውስጥ ግብት ይላል። ያገኘውን ሰባስቦ በጥድፊያ አጥሩን ጥሶ ሲወጣም በሰራ አካላቱ እሾህ ተከሰከሰበትና አረፈው ። ቆዳውን አልፎ ስጋው ላይ የተተከለ እሾህ እየጠዘጠዘ የሚቆም የሚቀመጥበትንም አሳጣው። ዝንጀሮ ሌላው ወገኑ ሲጠቃ እንደ አሁኑ ዘመን አብዛኛው ጠቢያዊ ዝም ብሎ የሚያይ አልነበረምና  ሌሎች ዝንጀሮዎች እሾሁን ሊነቅሉለት ብርር ብለው መጡለት። በደረሱለት ወገኖቹ የተደሰተው በእሾህ የተጠቃው ዝንጀሮም በለሆስታ "መጀመሪያ መቀመጫዬን" አላቸው ይባላል። "ይህንን ያለው የየትኛው ጎጥ ዝንጀሮ ነው?  የነቀሉለትስ  ከየትኛው ክልል የመጡ ዝንጀሮዎች ናቸው?" እያላችሁ መንፈስ-ቅዱስ በራቃቸው ጥያቄዎች አታዋክቡኝ። የዘመኑን የአንትሮፖሎጅስቶች የጥናት ውጤት በጥልቀት ባላውቅም እኔ አሁን ባለኝ ግንዛቤ የዝንጀሮ ቆሮ በፈንታው ሳይጋበዙ ጠቢያ ትከሻ ላይ እንደ ቆሌ ቁጢጥ ካሉት ከንቱዎች በአእምሮ ብስለት እጅግ ስለሚሻል ክልልና ጎጥ የሚሉት ቃላት ከአንደበቱ ወጥተው የሚያውቁ አይመስለኝም።*

*ከማንኛውም ሰው በተለየ መልኩ በተንኮል የደለቡ ሰው-መሳይ-ሰዎች የሚዘሩት ፍዳ እንስሳት ብቻ ላይ አላቆመም። የእኛኑ አገር እንደ ምሳሌ ብንወስድ ዛሬ የሰው ቀርቶ የአውሬው ሁሉ አእምሮ ፍሬ አፍርቶ መገዳደል ባቆመበት ዘመን እነዚህ ከንቱ ፍጡራን በራሳቸው አምሳል የተፈጠረውን የሰው ልጅ ንብረቱን እየገፈፉ፣ ከስራ እያባረሩ፣ ወህኒ ቤት እየዶሉ፣ አእምሮውንና አይኑን እየሸፈኑ፣ ጆሮውንና አፉን የእየወተፉ ያሰቃዩታል። ይህንን የሰቆቃ ኢፍትሐዊ ድንጋጌ ለመጣስ የሚዳዳውን ደግሞ በገዛ አገሩ እግር ተወርች አስረው ያሰቃዩታል ወይም በዚህም በዚያም ብለው ይሰውታል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ እንዲህ አይነቱን እሾህ ተከትለው የሚመጡት ሌሎች እንደ ችጋርና በሽታ ያሉ እሾሆችም ከእነዚህ ጋር ተዳምረው ከህጻን እስከ አዛውንት መከራውን ያበሉታል። እንዲያው በጠቅላላው የእኛ አገር ሕዝብ አካሉ ከላይ እስከታች እነዚህን በመሳሰሉ እሾሆች የተወረረ ነው። ተሸራሽቶ ቁጭ ብሎ የሚያስብበት፣ ሐሳቡን የሚገልጽበት፣ የሚወያይበት እንዲያውም ይህ ሁሉም ቀርቶ የእንሰሳ ያህል እንኳን ያለ ስጋት ተኝቶ የሚያድርበት አጋጣሚ ስለሌለው ሰቆቃ ቀቅሎ ሲበላው እርሱም ሰቆቃን እንደ እንጀራ ሲጎርስ ያድራል።*

*ግራ እሚያጋባው ጉዳይ ታዲያ እንዲህ አይነቱን እሾህ ከሕዝቡ ላይ ነቅለን እንጥላለን የሚሉት ሐይሎች አሰላለፍና አመለካከት ነው። አንዳንዶቹ መጀመሪያ እጅ ላይ ያለው እሾህ መነቀል አለበት ሲሉ ሌሎች ደግሞ የለም ጸጉር ላይ የተከሰከሰው በቅድሚያ ይወገድ በማለት ገና በሩቁ ዱላ ቀረሽ ጭቅጭቅ ሲፈጥሩ ያድራሉ። ሌሎች እንዲያውም ይባስ ብለው እሾሁን ለመንቀል አብሯችው በተሰለፈው እሾህ-ነቃይ ዜጋ ላይ ሌላ እሾህ እየተከሉ ክንዱን ሊያዝሉ ሲፍጨረጨሩ ይስተዋላሉ። በዚህ አይነት የውህደት ቀለበት ውስጥ ስንዞር ግማሽ ክፍለ ዘመን ሊሞላን ነው። ከፊሎቻችን የልፋታችንን ፍሬ ሳናይ አልፈናል፤ የተቀረነውም በከንቱ አርጅተናል። ከዚህ ውጪ ያለነውም ስለ እሾህ አወጣጥ ብዙ ልምድ የቀሰምን አንመስልም። ኢፍትሐዊነትና እርሱ የወለዳቸውን ችጋርና በሽታ የሚባሉ እሾሆች* በወረንጦ መንቀሉን ትተን የርስ በርስ ፍትጊያውን አንቧትረን በመቀጠል ላይ ያለን ብዙ አለን። በዚህም ምክንያት አብዛኛው ራሱን በእሾህ ነቃይነት የሚመድብ እርስ በርሱ እየተገፋፋ እነቅላለሁ ብሎ በሚመዘው እሾህ ሕዝቡን መልሶ እየወጋ የጠቢያን ሕዝብ ገላ ወንፊት በማድረግ ላይ ይገኛል። ሕዝቡም ብዙ በመጠቅጠቁ እንደ ልማድ ቆጥሮት ደንዘዝ ያለ ይመስላል።*

*"መጀመሪያ መቀመጫዬን" ብሏል ዝንጀሮ። እንደኔ እንደኔ የአገራችን ሕዝብም ሰሚ አጣ እንጂ "መጀመሪያ መቀመጫችንን !" እያለ ሲጮህ የኖረ ይመስለኛል። አዎ መጀመሪያ በተፈጠረበት ምድር ካለምንም ስጋት መኖርን ይመኛል ብዬ አስባለሁ። እርግጥ ነው እንደማንኛውም ሕዝብ አምላክ የሰጠውን ገላ ካለቅንጣት ገደብ፣ "አትተንፍስ፤ ከተነፈስክም*

በዚህ ህግና ደንብ መሰረት ተንፍስ” ከሚል ኢ.መለኮታዊ ድንጋጌ ውጭ መጠቀም እንደሚሻ አምናለሁ። አይኑ የተመኘውን እንዲያይ፣ ጆሮው የፈለገውን እንዲሰማ፣ አፍንጫው የሚጥመውን እንዲያሸት ቆዳውም የሻተውን እንዲዳስስ ይመኛል። ለኔ የሰው ወይም የሕዝብ መቀመጫው አጢሴ ብሎ ሲፈጠር ከፈጣሪ የተሰጠው፤ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን ፈጣሪን በሚቃረን እርጉም ሐይል የተገፈፈው ሰብአዊ መብት የሚባለው ጸጋ ነው። የመሬት ይዞታ፣ የንግድ ሥርዓት፣ የሕዝብ አደረጃጀት፣ አብሮ የመኖር ወይም ያለ መኖርና ሌላ ሌላውም ጉዳይ እሾሁ ተነቅሎለት በምቾት ተቀምጦ የሚያስብ፣ የሚመራመርና፣አራቱን የቋንቋ ክፍሎች( መስማት፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) ተጠቅሞ ሐሳቡን ካለምንም ገደብ መግለጽ የሚችል ሕዝብ የሚፈታው ጉዳይ ነው።

የዝንጀሮን እሾህ ያስወገደው ዝንጀሮ እንደሆነ ሁሉ በሰው ላይ የተተከለውን እሾህ መንቀል ያለበትም ሰው ነው። ሰው ደግሞ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ አኝዋክ፣ ዶርዜ፣ አማራ ወዘተ እየተባለ ሊከፈል የማይችል ሁለንተናዊ (universal) የሆነ ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ከዚህ ጽንሰ-ሐሳብ ላይ እሾሁ እስካልተነቀለ ድረስ የሰው ልጅ እንደ ደማ ይኖራል። በምቾት የሚኖሩ ጠቢያውያን በየምእራቡ አለም አደባባይ የሚጮሁት በወገናቸው ላይ የተተከለው እሾህ እነርሱንም እየወጋቸው ይመስለኛል። በዝንጀሮ ላይ የተከሰከሰን እሾህ ለመንቀል ያስፈለገው መመዘኛ ዝንጀሮ ሆኖ መገኘት ነበር። በሰው ላይ የተከሰከሰን እሾህ ለመንቀልም አነስታይ፣ ተባህት፤ ህጻን፣ አዋቂ፤ አማኝ ወይም እምነት-አልባ ሆኖ መገኘት አያስፈልግም። አዎን ከሰው ላይ እሾህን ለመንቀልና እግር ተወርች አስሮ በእሾህ ከሚያደማ ሐይል ሕዝብን ለመገላገል ሲዳማ፣ ትግሬ፣ ወላይታ፣ ከምባታ፣ ሸናሻ፣ አፋር ወዘተርፈ ሆኖ መገኘት አለዚያም የዚህ ወይም የዚያኛው ድርጅት አባል መሆን አያሻም። ራስን በተወሰነ ከንቱ-ሰው ሰራሽ ክልል ውስጥ ወስኖ የሰው ክፍልፋይ ከማድረግ ተቆጥቦ ሙሉሰው** ሆኖ መገኘት በቂ ነው። እሾህን ከሰው ወይም ከሕዝብ ላይ ሊነቅሉ ሲነሱም መነሻሸሙን ትቶ በአንድነት ከመሰረቱ፣ ከመቀመጫው መጀመር ነው። አመሰግናለሁ።

*ይድረስ ለእኛ- ለማንበብ ይህንን ይጫኑ http://www.quatero.net/meta/yidres.pdf

**ለመሆኑ ሰው ምንድነው? ለማንበብ ይህንን ይጫኑ http://www.addisvoice.com/article/sew2.pdf

*ጥር ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*